1/2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

ቁጥር
Ref.No. ዘ1-810 ሀ0250/
ቀን
Date. 8/7/2003

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA - ETHIOPIA

697/2013

**ለሕግ መምሪያ**
**ከ/ል/ኮ/ሚ**

ጉዳዩ፡- **የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ**፡

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች ለተመረጡ የሥራ ተቋራጮች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2003 የፀደቀውን ሰነድ ከታህሳስ 27 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን አባሪ በማድረግ ልከናል፡፡

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ
ሚኒስትር

**ግልባጭ**፡

- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ኮንስትራክሽን ዘርፍ/
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ከተማ ልማት ዘርፍ/

**ከ/ል/ኮ/ሚ**

ስልክ/ Tel.
011-553-16-88
011-553-16-72
011-553-16-73
የፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
24134/1000
ፋክስ /Fax
011-554-12-68
ድህረ ገጽ / Web Site
WWW.mudc.Gov.et
E-Mail: mwud_sm@ethionet.et

# በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች ለተመረጡ ሥራ ተቋራጮች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 697/2013

የካቲት 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


መመሪያ መግለጫ ..... 1
መመሪያ ቁጥር 1/2003 ..... 2
**ክፍል አንድ ..... 3**
**ጠቅላላ ..... 3**
1. አጭር ርዕስ ..... 3
2. ትርጓሜ ..... 3
**ክፍል ሁለት ..... 4**
**ስለምዝገባ ..... 4**
3. የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መሥፈርቶች ..... 4
4. የሥራ ተቋራጭነት ደረጃ ..... 5
5. የሥራ ተቋራጮች የምዝገባ ጥሪ ስለማድረግ ..... 6
6. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚደረገው ጥሪ ፡- ..... 6
7. ለምዝገባ ብቁ ያልሆኑ አመልካቾች ..... 6
8. የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ተቀባይነት ..... 7
9. የመረጣው ሥርዓት ..... 7
10. የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ..... 7
11. ህጋዊ ሰውነት ..... 8
12. የሥራ ተቋራጮች የፕሮጀክት መጠን ..... 8
13. የምዝገባ የምሥክር ወረቀትን ስለመሠረዝ ..... 8
14. የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ስለማገድ ..... 9
**ክፍል ሶስት ..... 10**
**የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ..... 10**
15. አቤቱታ ስለማቅረብ ..... 10
16. የኮሚቴው ስብጥር ..... 10
17. የሥልጣን ወሰንና የውሳኔ አሰጣጥ ..... 11
18. ወቅታዊ መረጃ ስለመስጠት ..... 12
19. ጥብቅ ክልከላ ..... 12
**ክፍል አራት ..... 12**
**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ..... 12**
20. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ..... 12
21. የማስፈፀም ኃላፊነት ..... 13
22. መመሪያውን ስለማሻሻል ..... 13
23. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ..... 13



አዲስ አበባ

# ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች ለተመረጡ ሥራ ተቋራጮች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣው መመሪያ መግለጫ

የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና መሰል አገር አቀፍ ሽፋን ያላቸው የመንግሥት ፕሮጀክቶች የሥራ ተቋራጮች እጥረት እንዳይገጥማቸው ለማድረግ ባለሙያዎችን መርጦ ለሥራ ተቋራጭነት ለማብቃት በተዘጋጀው ፕሮግራም መሠረት መመሪያ በማዘጋጀት፣ ባለሙያዎችን በመመዝገብ፣ በመምረጥ፣ በማሰልጠን እና ትስስር በመፍጠር ቁጥራቸው ከ750 በላይ የሚሆኑ ባለሙያዎች ወደ ሥራ መግባታቸው እና የሚያበረታታ አፈፃፀም የተመዘገበ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የተጠቀሰው ቁጥር ያላቸው ሥራ ተቋራጮች የተመረጡት በአገር አቀፍ ደረጃ በተጀመሩት እና በመከናወን ላይ በሚገኙት፤

- ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም፣
- ለጤና ጣቢያዎች ግንባታ፣
- ለቴሌኮም የሞባይል ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች፣
- ለሬዲዮ ማስፋፊያ ፕሮጀክት
- ለተንዳሆ ስኳር የቤቶች ልማት ፕሮጀክት

እንዲሳተፉ ታስቦ የነበረ ሲሆን በዚህም የተነሣ ሥራ ተቋራጮቹ እንዲያገኙ የተደረገው የምስክር ወረቀት ተሳትፏቸውን በነዚህ ግንባታዎች ብቻ የሚወስን ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሲገነቡ የታቀዱት ጤና ጣቢያዎች በሙሉ ሥራ ተቋራጮች የተመደቡላቸው በመሆኑ፣ የሞባይል ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችም ከአንድ የግንባታ ዙር በኋላ የሚጠናቀቁ በመሆኑ እና በቤቶች ልማት ፕሮጀክት የሚሸፈኑ ከተሞች ቁጥር የሚጨምር ባለመሆኑ የተመረጡትን ሥራ ተቋራጮች ከተጠቀሱት ፕሮጀክቶች ጋር ብቻ በማስተሳሰር መቀጠል አስፈላጊ የማይሆንበት ደረጃ ተደርሷል፡፡ ከዚህም የተነሳ ሥራ ተቋራጮቹ በሌሎች የግንባታ ቦታዎችም ተወዳድረው መሥራት የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸት አስፈልጓል፡፡

በዚህም መሠረት ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች መሰል የመንግሥት ፕሮጀክቶች ባለሙያዎችን መርጦ ለሥራ ተቋራጭነት ለማብቃት በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት የተመረጡት እና ወደ ሥራ የገቡት ባለሙያዎች በማንኛውም ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍ እንዲችሉ ለማድረግ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 25/1/ቸ/ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች ለተመረጡ ሥራ ተቋራጮች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 697/2013

የተቀናጀ የቤቶች ልማት ኘሮግራም እና መሰል አገር አቀፍ ሽፋን ያላቸው የመንግሥት ኘሮጀክቶች የሥራ ተቋራጮች እጥረት እንዳይገጥማቸው ለማድረግ ባለሙያዎችን መርጦ ለሥራ ተቋራጭነት ለማብቃት በተዘጋጀው ፕሮግራም መሠረት መመሪያ በማዘጋጀት፣ ባለሙያዎችን በመመዝገብ፣ በመምረጥ፣ በማሰልጠን እና ትስስር በመፍጠር ብዙ ቁጥር ያላቸው ሥራ ተቋራጮች ወደ ሥራ በማግባታቸው የሚያበረታታ አፈፃፀም የተመዘገበ ቢሆንም ሥራ ተቋራጮቹ እንዲያገኙ የተደረገው የምስክር ወረቀት በውስን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የነበረ በመሆኑ የእነዚህ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ በቂና ቀጣይ ሥራ ሊያስገኙላቸው የማይችሉ መሆኑ ከወዲሁ የታመነበት ስለሆነ፤

በአሁኑ ወቅት የፀደቀውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተከትሎ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ሊከናወኑ የታቀዱትን ትላልቅ ፕሮጀክቶች ሊያስተናግዱ የሚችሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሥራ ተቋራጮች ከመፍጠር አንጻር እስካሁን በመንግሥት ፕሮጀክቶች ታቅፈው ሲሠሩ የነበሩትንና ብቃታቸው የተመሠከረላቸውን ሥራ ተቋራጮች ከፍ ወዳለ ደረጃ በማሳደግና የሥራ ሥምሪታቸውንም ክልል ማስፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዚህም መሠረት ሥራ ተቋራጮቹን ቀደም ሲል በሚሠሩባቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሳይወሰኑ በማንኛውም ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍ በሌሎች የግንባታ ቦታዎችም ተወዳድረው መሥራት የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸትና አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 25 /1/ /ቸ/ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።



የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ " ለተመረጡ ሥራ ተቋራጮች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣ መመሪያ ቁጥር 697/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1/ "ሥራ ተቋራጭ" ማለት ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች መሰል የመንግሥት ፕሮጀክቶች የግንባታ ባለሙያዎችን መርጦ ለሥራ ተቋራጭነት ለማብቃት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በተዘጋጀው የ2003 ዓ.ም መመሪያ መሠረት ተመርጦ ሥልጠና የወሰደ እና የሥራ ትስስር የተፈጠረለት ባለሙያ ነው።

2/ "የባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ" ማለት ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ለሌሎች የመንግሥት ፕሮጀክቶች ግንባታ ባለሙያዎችን መርጦ ለሥራ ተቋራጭነት ለማብቃት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የወጣው የ2000 ዓ.ም መመሪያ ማለት ነው።

3/ "መመሪያ" ማለት ይህ ለተመረጡ ሥራ ተቋራጮች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2003 ነው።

4/ "የሥራ ተቋራጭ ደረጃ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 471/98 ለሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ወይም በአዋጅ ቁጥር 691/2003 ለሚኒስቴሩ የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት በማድረግ የተሰጠ ወይም የሚሰጥ የሥራ ተቋራጭነት ደረጃ ነው።

5/ "የተገደበ የምዝገባ ምስክር ወረቀት" ማለት በባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ መሠረት በውስን ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሰሩ ተመልምለው ለሠለጠኑ የሥራ ተቋራጮች የተሰጠው ወይም የሚሰጠው የምሥክር ወረቀት ነው ፤



የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ... አገልግሎት ክፍል

6/ "ያልተገደበ የምዝገባ ምስክር ወረቀት" ማለት ሥራ ተቋራጮች በባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ በተፈቀዱላቸው ፕሮጀክቶች ሳይወሰኑ ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው ሌሎች ፕሮጀክቶች ሁሉ ለመሳተፍ እንዲችሉ የሚሰጥ የሥራ ተቋራጮች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማለት ነው፡፡

7/ "አጠቃላይ መመሪያ" ማለት ከባለሙያዎች ማብቂያ መመሪያ ውጪ ለሚስተናገዱ የህንፃ ሥራ ተቋራጮች ተፈጻሚ የሚሆነው የምዝገባ መመሪያ ነው፤

8/ "መዝጋቢ አካል" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የሚመዘገቡ አመልካቾችን ማመልከቻዎች በመቀበልና በመመርመር ለአመልካቹ የምሥክር ወረቀት እንዲሰጠው ወይም እንዳይሰጠው እንዲሁም የዲሲፕሊን ጉድለት ሲከሰት የምሥክር ወረቀቱ እንዲሠረዝ የሚወስን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የሥራ ሂደት ወይም ቢሮ ነው፤

9/ "ኮሚቴ" ማለት መዝጋቢው አካል የምዝገባ የምሥክር ወረቀት በመስጠት ሂደት የትምህርት ዝግጅቱ የሥራ ልምዱ ወይም እነዚህን የሚያመለክቱ ሌሎች ማስረጃዎችን ባለመቀበል አመልካቹ የምሥክር ወረቀት እንዳይሰጠው፣ ወይም በዲሲፕሊንና በሌሎች ምክንያቶች የተሰጠው የምዝገባ የምሥክር ወረቀት እንዲሠረዝ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ፣ እንዲሁም በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠበት የዕገዳ ትዕዛዝ እንዲነሳ የሚቀርበውን ቅሬታ ተቀብሎ የሚያስተናግድ አካል ነው ፤

10/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለምዝገባ

### 3. የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መሥፈርቶች

በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ የሚሆኑት በባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ መሠረት የተመረጡ ሥራ ተቋራጮች ሲሆኑ በዚህ መመሪያ መሠረት ያልተገደበ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1/ የሥራ ትሥሥር በማድረግ በባለቤትነት ፕሮጀክቶቹን ሲያካሂዱ ከቆዩ አሠሪ መስሪያ ቤቶች ወይንም የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች መልካም የሥራ አፈፃፀም የነበራቸው ስለመሆኑ ፤

2/ ከአሠሪ መሥሪያ ቤቶቻቸው ብድር አለመውሰዳቸውን፣ ወይም ብድር ወስደው በብድር ስምምነቱ መሠረት እየከፈሉ ስለመሆኑ ፣

3/ በባለሞያዎች የማብቂያ መመሪያ የተመለከተውን የባለሞያና የማሽነሪ በብቃት ስለማሟላታቸው፣

4/ በሚኒስቴሩ በኩል በተመቻቸው የብድር ሥርዓት ወይንም ከፕሮጀክት በተገኘ ፋይናንስ በባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ እንዲሟሉ የተቀመጡትን መስፈርቶች ስለማሟላታቸው ፣

5/ ታክስና ከታክስ ጋር የተገናኙ ግዴታዎችን ስለመወጣታቸው፣

ማስረጃ የሚያቀርቡ መሆን ይኖርባቸዋል።

## 4. የሥራ ተቋራጭነት ደረጃ

1/ ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጠው የተቋራጭነት ዓይነት እና ደረጃ የጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት ደረጃ 6 ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር /1/ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ይህ መመሪያ በአጠቃላይ መመሪያው የሥራ ልምዳቸውና የማሽነሪ ይዞታቸው ለጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት የሚያበቃቸው ሥራ ተቋራጮች ከደረጃ 6 በላይ የጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ከማግኘት አይከለክላቸውም። ሆኖም ሥራ ተቋራጮቹ በተመሣሣይ ጊዜ ውስጥ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠውን የምሥክር ወረቀትና በአጠቃላይ መመሪያው መሠረት የሚሰጠውን የምሥክር ወረቀት ይዘው ሊሠሩበት አይችሉም ።

3/ ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጠው የተቋራጭነት ዓይነት እና ደረጃ የሥራ ተቋራጮቹን የሥራ አፈጻጸምና የማሽነሪ አቅም ተከትሎ የሚሻሻል ይሆናል።

## 5. የሥራ ተቋራጮች የምዝገባ ጥሪ ስለማድረግ

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት ተመልምለው ለሚመረጡ ሥራ ተቋራጮች ከዚህ በታች ተዘርዝረው የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ የማስታወቂያ ጥሪ ይተላለፋል።

2/ የማስታወቂያ ጥሪው በተቻለ መጠን ለሁሉም ተደራሽ ይሆን ዘንድ ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው መንግስታዊ የዜና ማሰራጫዎች በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ መተላለፍ ይኖርበታል ።

3/ በጥሪው መሠረት ለሚቀርቡ ባለሞያዎች የተሻለ ዕድል ለመስጠት የምዝገባው ጊዜ የሁሉንም የሀገሪቱን ክልል ርቀትና የትራንስፖርት ሁኔታ ከግምት ያስገባ መሆን ይገባዋል።

## 6. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚደረገው ጥሪ ፡-

1/ ስለጥሪው ዓላማ ፣

2/ በመመሪያው መሰረት ባለሞያዎችን ለመመዝገብ ማሟላት ያለባቸውን የሙያና የማቴሪያል ዝግጅቶችን ፣

3/ መሥፈርቶቹን አሟልተው ለሚመረጡ ሥራ ተቋራጮች ስለሚደረገው የግብዓትና የሥልጠና ድጋፍ ፣

4/ ምዝገባ የሚካሄድባቸውን ቦታና ጊዜ ፣

5/ በአመልካቾች መቅረብ የሚገባቸውን ማስረጃዎች ዝርዝር፣

6/ በጥሪው መሠረት ተወዳዳሪዎች ስለሚያቀርቧቸው የሥራ ልምድ ማስረጃዎች የሚገልፅ መሆን ይኖርበታል ።

## 7. ለምዝገባ ብቁ ያልሆኑ አመልካቾች

ማንኛውም ለሥራ ተቋራጭነት ለመመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ፣

1/ የትምህርት ዝግጅቱ ወይም የሥራ ልምድ ወይም የማሽነሪ አቅም ማሳያ ማስረጃው በማታለል ተግባር ወይም በሐሰት የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ አግባብ ባለው ህግ መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የምዝገባ ጥያቄው ተቀባይነት አይኖረውም።

2/ አመልካቹ መሥራት የማያስችለው የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለበት በመሆኑ ሥራውን ሊያከናውን አይችልም ተብሎ ሲታመን ወይም ይህ መመሪያ የሚጠይቀውን መስፈርት የማያሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ የምዝገባ ጥያቄው ተቀባይነት አይኖረውም ።

## 8. የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ተቀባይነት

1/ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ ማንኛውም ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ እንዲሁም ከግሉ ዘርፍ የሚመጡ የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

2/ አመልካች ባለሙያዎች የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ለአመልካቾች በተዘጋጀላቸው የምዝገባ ቅጽ ላይ በፊርማቸው የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው።

## 9. የመረጣው ሥርዓት

1/ መዝጋቢው አካል ለመረጣ በተዘጋጀው የመምረጫ መመሪያ መሠረት የተመዘገቡ ባለሙያዎች ያቀረቧቸውን ሰነዶችን የማጣራት እና መስፈርቶቹን ያሟሉትን የመምረጥ ሥራ ያከናውናል።

2/ የመረጣው ሥራ ሲጠናቀቅ መዝጋቢው አካል በመሥሪያ ቤቱ ግቢና በምዝገባው ሂደት ተሳታፊ በነበሩ የክልል ቢሮ መ/ቤቶች ውስጥ በግልፅ በሚታይ ሥፍራ መለጠፍ ይኖርበታል።

3/ ከመረጣው ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያላቸው አመልካቾች ቅሬታቸውን ውጤቱ በማስታወቂያ የተለጠፈበት ቀን ማግሥት ጀምሮ በሚቆጠር አሥር ቀን ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 ለተመለከተው ኮሚቴ ቅሬታቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ።

## 10. የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1/ ከዚህ በላይ በአንቀጽ በተመለከተው መሠረት የተመረጡ ሥራ ተቋራጮች በዚህ መመሪያ መሠረት ለደረጃቸው የሚፈቀደው የሥራ ተቋራጭነት የምሥክር ወረቀት ይሰጣቸዋል ።

2/ በዚህ መመሪያ መሠረት ለተመረጡ ሥራ ተቋራጮች የሚሰጠው የሥራ ተቋራጭነት የምሥክር ወረቀት ምንም ዓይነት ገደብ አይጻፍበትም ።

3/ በዚህ መመሪያ መሠረት የተመረጡ ሥራ ተቋራጮች በባለሙያዎች ማብቂያ መመሪያ መሠረት የተሰጣቸውን የምሥክር ወረቀት መመለስ ይኖርባቸዋል።

## 11. ህጋዊ ሰውነት

1/ የተመረጠው ሥራ ተቋራጭ ህጋዊ ሰውነት የሚያገኘው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ሲመዘገብ ነው።

2/ ሥራ ተቋራጩ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚኖረው ግንኙነት በተመዘገበበት ሰነድ የሚወሰን ይሆናል።

## 12. የሥራ ተቋራጮች የፕሮጀክት መጠን

ሥራ ተቋራጮች ሊይዙት የሚችሉት የአንድ ፕሮጀክት መጠን በባለሙያዎች ማብቂያ መመሪያ ውስጥ ለሚካተቱ ፕሮጀክቶች በባለሙያዎች ማብቂያ መመሪያው በተመለከተው መሠረት ሲሆን ከነዚህ ውጪ ባሉ ሌሎች ፕሮጀክቶች የሚሳተፉት በአጠቃላይ መመሪያው መሠረትና በተሰጣቸው ደረጃ ይሆናል ።

## 13. የምዝገባ የምሥክር ወረቀትን ስለመሠረዝ

ማንኛውም በዚህ መመሪያ መሠረት ለሥራ ተቋራጭ የተሰጠ የምዝገባ የምሥክር ወረቀት፣

1/ የትምህርት ዝግጅቱ ወይም የሥራ ልምድ ወይም የማሽነሪ አቅም ማሳያ ማስረጃው በማታለል ተግባር ወይም በሐሰት የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

2/ በማናቸውም መንገድ ለሌሎች መጠቀሚያ ተላልፎ መስጠቱ ሲረጋገጥ ፤

3/ አመልካቹ መሥራት የማያስችለው የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለበት በመሆኑ የሚሠማራበትን ሥራ ውጤታማ እያደረገውም ተብሎ የሚታመን ሲሆን ወይም ይህ መመሪያ የሚጠይቀውን ሌላ መስፈርትም ያላሟላ ሆኖ

ሲገኝ፣ የተሰጠው የምዝገባ የምስክር ወረቀት በመዝጋቢው አካል ሊሰረዝ ይችላል ።

## 14. የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ስለማገድ

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ያልተገደበ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሥራ ተቋራጭ የምስክር ወረቀቱን ካገኘ በኋላም ከሥራ አፈጻጸም ጋር የተገናኘ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ወይም አቤቱታ ሲቀርብበት ሥራ ተቋራጩ የተነገረበትን ጥፋት ስለመፈፀሙ እስኪጣራ ድረስ መዝጋቢው አካል ለሥራ ተቋራጩ የተሰጠውን የምስክር ወረቀት ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያግደው ይችላል ።

2/ ሆኖም መዝጋቢው አካል የምሥክር ወረቀቱ እንዲታገድ በተደረገ ሥራ ተቋራጭ ጉዳይ ላይ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

3/ መዝጋቢው አካል በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ስለዕገዳው መነሳት ወይም ሌላ ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ ይህንኑ ውሳኔ ለባለጉዳዩ በጽሁፍ መስጠት ወይም በመሥሪያ ቤቱ በግልፅ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት ።

4/ በዚህ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠ እንደሆነ ይህ ጊዜ ሲጠናቀቅ በሚቀርብለት ማመልከቻ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ዕገዳዉ ወዲያውኑ እንዲነሳ ይወስናል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት ዕግድ የተሰጠበት ሥራ ተቋራጭ የዲሲፕሊን ጉዳይ በፌዴራል የግዥ ኤጀንሲ የሚታይ ሆኖ ሲገኝ መዝጋቢው አካል በዚሁ የዕገዳ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ለኤጀንሲው መላክ አለበት።

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት በሚሰጥ ዕገዳ ላይ አቤቱታ አይቀርብበትም።

7/ የሥራ ተቋራጩ ፈቃድ በአንቀጽ 13 ንዑስ ቁጥር /1/ሀ/ መሠረት እንዲሠረዝ ሲወሰን ጥፋተኛው በሕግ እንዲጠየቅ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል መተላለፍ አለበት።

## ክፍል ሶስት
## የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

### 15. አቤቱታ ስለማቅረብ

1/ ለሥራ ተቋራጭነት ተወዳድሮ ያልተመረጠ ወይም የተሰጠው የምሥክር ወረቀት በዲሲፕሊን ወይም በሌላ ምክንያት እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል የተወሰነበት ወይም በአንቀጽ 14/4/ በተመለከተው ሁኔታ ዕገዳው እንዲነሳለት የሚጠይቅ አመልካች መዝጋቢው አካል በሠጠው ውሳኔ ላይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 መሠረት ለሚቋቋመው ኮሚቴ ውሳኔው ወይም ዕገዳው አግባብ ያልሆነበትን ምክንያት በመግለፅ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

2/ አመልካቹ ለኮሚቴው ቅሬታውን ማቅረብ የሚችለው አለመመረጡ ከተገለፀበት ወይም ከመዝገብ እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል ውሳኔ በተሰጠ ወይም ውሳኔው በማስታወቂያ ከተገለፀ ማግሥት ጀምሮ በሚቆጠር በ10 ቀናት ውስጥ ይሆናል።

3/ ሆኖም በአንቀጽ 14 /2/ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ጉዳዩ ውሳኔ ያልተሰጠው ወይም ለኤጀንሲው ያልተላከለት ወይም ዕገዳ ያልተነሳለት አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳይገታ በማንኛውም ጊዜ ጥያቄውን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ሊያቀርብ ይችላል።

### 16. የኮሚቴው ስብጥር

1/ ኮሚቴው በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አማካኝነት የሚቋቋም ሆኖ 3 አባላት ያሉት ሲሆን፣ ስብጥሩም

ሀ) የከተማ ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ተወካይ............... ሰብሳቢ

ለ) የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ቢሮ ተወካይ ....... አባል

ሐ) የሕግ አገልግሎት መምሪያ ተወካይ ..................... አባል

የሚገኙበት ይሆናል።

2/ ኮሚቴዉ አብላጫ ድምጽ የሚሰጠው ውሳኔ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡ ድምፅ እኩል ለእኩል ሲሆን በሰብሳቢው ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡

3/ አግባብ ያለው የሥራ ሂደት ለኮሚቴው በፀሀፊነት የሚያገለግል ሠራተኛ ይመድባል፡፡

## 17. የሥልጣን ወሰንና የውሳኔ አሰጣጥ

ኮሚቴው

1/ አንድ ሥራ ተቋራጭ በማናቸውም ምክንያቶች ባለመመረጡ ወይም የአመልካቹን ማስረጃዎች ባለመቀበል የምሥክር ወረቀት እንዳይሰጠው መዝጋቢው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ፣

2/ እንዲሁም በአንቀጽ 14 /2/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠበት የዕገዳ ትዕዛዝ እንዲነሳ፣

የሚቀርበውን ቅሬታ ተቀብሎ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት፣

3/ ሥራ ተቋራጩ በሥራው ሂደት ወቅት በሚፈጽመው የዲሲፕሊን ጉድለት ከምዝገባ እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል ሲወሰን የሚቀርበውን ቅሬታ ተቀብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳ ፣እንዲፀና ወይም እንደገና እንዲታይ ለሚኒስትሩ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ፤

ሥልጣን ይኖረዋል ፡፡

4/ ኮሚቴው የቀረበለትን ዉሳኔ መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ የሚረዱ ማናቸውም ሰነዶችና ማስረጃዎችን በመስሪያ ቤቱ በኩል ማስቀረብና ማየት ይችላል፡፡

5/ ሚኒስትሩ የአመልካቹ ፈቃድ እንዲሰረዝ በኮሚቴው የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ የሚቀበለው ሲሆን የአመልካቹ ፈቃድ እንዲሠረዝ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 18. ወቅታዊ መረጃ ስለመስጠት

መዝጋቢው አካል በማንኛውም ጊዜ በሥራ ተቋራጩ ላይ የተወሰዱ እርምጃዎችንና የተሰጡ ውሳኔዎችን እየተከታተለ ለሚመለከታቸው አካላት ወቅታዊ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት።

## 19. ጥብቅ ክልከላ

1/ ማንኛውም በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት የምሥክር ወረቀቱ የታገደበት ወይም የምሥክር ወረቀቱ የተሠረዘበት ሥራ ተቋራጭ የምሥክር ወረቀቱ ታግዶ ባለበት ወይም ተሠርዞ ባለበት ጊዜ ውስጥ ከመዝጋቢው አካል በልዩ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ መሠረት የተፈቀዱ ሥራዎችን ሊያከናውን አይችልም ።

2/ መዝጋቢው አካል የምሥክር ወረቀቱ የተሠረዘበት ወይም የታገደበት ሥራ ተቋራጭ የምሥክር ወረቀቱ ተሠርዞ ወይም ታግዶ ባለበት ወቅት በዚህ መመሪያ መሠረት በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ተመርኩዞ ባወጣው የንግድ ፈቃድ ሲንቀሳቀስ በሚገኝ ሥራ ተቋራጭ ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አግባብ ላለው አካል ማስተላለፍ አለበት ።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 20. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ አግባብነት ያላቸው የባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ፤ እንዲሁም ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በማሟያነት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 21. የማስፈፀም ኃላፊነት

የሚኒስቴሩ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ይህን መመሪያ የማስፈፀም ኃላፊነት ተሰጥቶታል ።

## 22. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።

## 23. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት __ ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።

አዲስ አበባ የካቲት __ ቀን 2003 ዓ.ም

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

ሚኒስትር